## *ለምንገነባው የፍቅር ድልድይ የሚጠቅም ሃሳብ አለኝ*

*መኮንን ሻውል ወልደጊዮርጊስ*

*ሰው ማሰቡን የሚያቆመው ሲሞት ብቻ ነውና ሃሰቡን ለመሰሎቹ በማካፈሉ የሚወገዝበት ዘመን ማክተሙን ፣ ክቡር ጠቅላይ ሚኒሥተራችን ፣ ዶ/ር አብይ አህመድ ከቃል በላይ በትግባር ዕውን እነዲሆን ከመላው ኢትዮጵያዊያን ጋር እንደሚሰሩ በማረጋገጣቸው በእጅጉ ተደስቻለሁ።*

***" ለምን ታስባለህ? ሃሰብህንስ ለምን ታካፍላለህ ?"በማለት የሚገድበው ሳይኖር ፤"ህዝብን ታነቃለህ፣የግለሰብን ህሊና በማንቃትና የግንዛቤ እጥረቱንም በመቅረፍ፣በድምርም ህዝብ እንከኔን እንዲያይ በማደረግ ህግ እና ህገመንግስት እኔ ራሴ ሆኜ ሳለ፣ህገመንግስቱን ጥሰሃል፣በሥልጣንም ያለአግባብ ባልገሃል፣በማሰኘት እንደጠላ ታደርጋለህ።...አንተ እኔ ህዝብን እንዳሻው እየመራው የምሰራው ሥራ የማይታይህ ፀረ-ልማትና ፀረ-ህዝብ ነህ።ፀረ ህገመንግስት ነህ።ወዘተ።በማለት ሰዎች በሰብአዊ እና ዴሞክራሲያዊ መብታቸው እነዳይጠቀሙ የሚያደርግ ሥርአት አክተሞል። እነዚህ "ሊበልዋትን ያሰቧትን አሞራ ጅግራ ይሏታል። በሚል ቅኘት የሚጓዙናየሚገዙ ሸባቢ መንግስታዊና ሥልጣናዊ አሰተሳሰቦችና ድረጊቶች በዚህ በዲጂታል(አለም በቴክኖሎጂ ተራቆ አለም በጠበበችበት ዘመን)ላይመለሱ ተሰናበተዋል።"** *በማለት የልብ ልብ ለዴሞክራሲ ርሃብተኞች ሰጥተዋል።በርግጥም እንዳንናገር የሥልጣን አለንጋ ይዞ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ "**ዋ !ውርድ ከራሴ**..." በማለት የሚየሥፈራራን፣የሥልጣን ጠመንጃ ዛሬ የለም። ነገ እንደሚከሰት ግን ምንም ማረጋገጫ የለንም።*

*ግን፣ግን፣ለሰው ተፈጥሯዊ **ነፃነቶች(ለመናገር፣ለመስማትና፣ለማየት ነፃነቶች**) "ደንታ የለንም። የሚሉ በዚች ሀገር በመንግስት ሥም ከሌሉ መጪው የኢትዮጵያ ዜጎች ህይወት ደሥታው የበዛ እነደሚሆን ከወዲሁ መመሥከር እንችላለን።*

*ህይወት በደስታና በሥቃይ መሞላቷ እርግጥ ነው። ነገርግን ደሥታችን ይበዛ ዘንድ ፣ሁላችንም ሰው መሆናችንን በቅድሚያ ማመን ይኖርብናል።ዜጎች ይህችን በደሥታና በሥቃይ የተሞለች አጭር ህይወት ደስታዋን የሚበዙት ከሁሉ በፊት ሰው መሆናቸውን ሲገነዘቡ ብቻ ነው። ሰው መሆናቸውን እና ከሌላው ሰው ፈፅሞ የማይበልጡና የማያንሱ አለመሆናቸውን*

*መረዳት ይኖርባቸዋል።ሀብታም ሆኑ ደሃ፤ሥልጣን ኖራቸው አልኖራቸው ሁሉም ሰው እና ነገ አፈር የሚሆኑ ናቸው።የመሞት የመበስበስና ከምድር ህይወት የመፋቅ ዕጣ ፈንታ የሁሉም ነው።*

*ይህንን እውነት በማሳወቅና፣ሰው መሆናቸውን ተገንዝበው ሰውን በየሀገራቸው አስጠግተውና ዜግነት ሰጥተው በታላቅ እእምሮው በመጠቀም ሀገራቸውን እነድተበለፅግና ታላቅ ሀገርም እነድተሆን ያደረጉትን እና በማደረግ ላይ ያሉትንም የበለፀጉትንም ሀገሮች በማስተዋል በመመልከት የኢትዮጵያ ምሁራን ፣ዜጎችን በማንቃትና ሰው መሆናቸውን በማሰወቅ፣ ይህችን አጭር ህይወት በመገዳደል የበለጠ ለማሳጠር መቀዥቀዣቸውን እንዲያቆሙ ማደረግ ይጠበቅባቸዋል።*

*ለዚች ሀገር ታላቅነት ዜጎች በተሰማሩበት የሥራ መሥክ ሁሉ ጠንከረው በመሥራት በድምር ውጤት ለመላው ኢትዮጵያዊያን ብለፅግናን አውረሰው ማለፍ እነደሚገባቸው አበክረው እነዲያስቡ ባገኙት መድረክ ሁሉ መምከርና መዘከርም ሳይማር ያስተማራቸው ህዝብ እነደውለታ የሚቆጥረው ነው።*

*በሀገራችን የሚገኙ ብሄሮችና ብሄረሰቦች ሁሉ የተለያየ ቋንቋ እና ባህል፣እምነትናኃይማኖት ወዘተ።ቢኖራቸውም ፤መልካቸው ቢለያይም ፤ሁሉም የወል ሥም ያላቸው አንድ ፍጥረት ናቸው።እሱም "ሰው" ይሰኛል። ይህንን በቅጡ ሳይገነዘቡ ዘመናትን ቆጥረዋል። በ21ኛው መከዘ እንኖራለን ይላሉ እንጂ ከቆዳ ማወደድ ዘመን ከዘመነ መሳፍነት አስተሳሰብ ገና አልተላቀቁም። ዛሬም ሙሉ ለሙሉ የሰው ሰውነት የማይታወቅበት እና ቆዳውን የሚያዋድድ ማህበረሰብ በመላ ሀገሪቱ እዘና እዚህ መኖሩ ይታወቃል ።መላው አፍሪካም ከዚህ ኋለ ቀር ፈፅሞ አልተላቀቀም።*

*በዚህ ሰበብም፣ መንግስታቱ ሰውን በራሳቸው ርዕዮት ለማስጓዝ አለንጋን እንደብቸኛ አማራጭ ይጠቀሙበታል። መንግስት የተባለው አሥተዳዳሪ አካል፣አለንጋን እነደብቸኛ አማራጭ የሚጠቀምበት ከሆነ ከሚያሥተዳድረው ህዘብ ጋር ብዙ እርቀት ለመጎዝ አይችልም።ይሁን እነጂ የመንግስት አለንጋ ህዝብ ያመነበትን የሀገሪቱን ህግ ለማስከበር የሚገለግል፣በሀዝብ ቅቡልነት ያለውን በፍትህ፣በዴሞክራሲና በመልካም አስተዳደር ማቀፍ ውስጥ ያለና የይስሙላ ያልሆነ ፣መንግስትን የሚቆጣጠር መሳርያ ከሆነ፣ያለንጋው መኖር ጠቃሚ እንጂ ጎጂ አይሆንም።*

*በእረግጥ ለዘመናት ሰዎች ባሰለፉት የሰው ልጅ ታሪክ ውሰጥ መንግስት የተባለው ተቋም ህግ አልቦ አርጩሜና ኃይለኛ ገራፊ ነበረው፡፡ኢፍትሃዊነትና አባቱ ዳኛ ልጁ ቀማኛ የሆነበት መንግስትም በአፍሪካ ተንሰራፍቶ ይታይ ነበር፡፡ህግ ለሁሉም እኩል አልነበረም፡፡ህግ ገዢዎች የሚፈሩት የበላያቸው ፈፅሞ አልነበረም፡፡ የገዢዎች የበላይነት እንጂ!!*

*(በመንግስቱ ለማ ግጥም "የአንበርብር ጎሹን ሞት ሰበብ አንዘነጋውም፡፡"አንድ ኮማሪትን ለንጉስ ለአንድ ቀን አዳር በመመኘቱ ነበር፣ በሰላይ ተይዞ እነዲገረፍ የተፈረደበት፡፡የተፈረደበት ሰለሳ ጅራፍ ነበርና ሰላሳው ሳይሞላ ነው እዛው ፈግም ያለው፡፡)*

## ያኀበርብር፡ጐሹ፡ሞት።

ኧረ፡ስንቱ፡ስንቱ፡ናቸው፡የሞቱቱ፡
ለንጉሣቸው፡ክብር፡ለባንዲራይቱ።

እስኪ፡ብኒሣሣው፡እንበርብር፡ጐሹን፡
በደራ፡አደባባይ፡የወደቀውን፡
ያን፡ጠይም፡መዘዞ፡
ያን፡ወጣት፣ያን፡ሎጋ፡
የመርን፡ጐሹን፡ልጅ።

እሱስ፡ሆኖ፡አይደለም፡ታሪክ፡ቅዱስ፡
መጽደቂንም፡እንጂ፡ያቺ፡ያኀበርብር፡ነፍስ።

የሚያዘወትራት፡ያኀበርብር፡ወዳጅ፡
ነበረቹው፡አንዲት፡ቀይ፡ቆንጆ፡ልጅ።
ሴትኛ፡አዳሪ፡ናት፣
እሱም፡አላገባ።
ቀሳሚው፡ቢበዛም፡ይህቹኑ፡አበባ፡
«እያ፡ማር፡ወለላ፡እያ፡ማር፡እሸት»
እሱ፡ብቻ፡ነበር፡የእሳቲቱ፡እራት።

ቢገባም፡በሌሊት፣ቢወጣም፡በጧት።
በር፡ይመታል፡ሲያውቀው፡እንደማከፈት፡
ይለምናል፡አምኖ፡እምቢ፡እንዳሉት።

ከዕለታት፡አንድ፡ቀን፡በሰዓቱ፡ማታ፣
ክፈች፣ክፈች፣ብሎ፡ሳንቃውን፡ቢመታ፣
ወይ፡የሚለው፡አጣ፡
ገጠመው፡ዝምታ።

ደጋግሞም፡ቢጣራ፣ሰጠቹው፡መልሱን፦
እጁ፡ከ፡ሰው፡ወርሣታል፡የሱን፡ቦታውን።
«ይልቅ፡ልተኛበት፡»አለቹው፡«አትጩህ!»
ዲግም፡በር፡እስመታው፡መጣውና፡እልህ።

«ዋ፣በንጉሡ፡አምላክ!
አብዷል፡ሰክሯል፡እንዴ?



ነው፡እንጂ፡በውዴ፣አይደለም፡በግዴ።
ወጊድ፤በንጉሡ፡አምላክ!
አትግባ፡በንግዴ።»

እሱም፡ተስፋ፡ቆርጦ፡ሲሄድ፡ለመረቃት፤
ለንጉሡ፡ተመኛት፡ለዚያን፡ቀን፡ሌሊት።

ምርቃቱም፡ሆኖ፡ወንጀል፡ኀጢአቱ፡
ከዳኛ፡ፊት፡ቢቀርብ፡ወዲያውኑ፡በሣልስቱ፡
አርባ፡ጅራፍ፡ሆነ፡ሕገኛው፡ቅጣቱ።
ሞራ፡ሲጠጣ፡ ነው፡የቀለ፡ጅራፉ፡
ብቻ፡አላርፍም፡አለ፡የገረፈው፡እፉ፤

«ዓይንህን፡ተጠንቀቅ፣ወንድም፣አደራህን፤
እንደላጐድልብህ፡በከንቱ፡አካልህን።»

ምፀቱ፡ገደለው፣
እዚያው፡ግጥም፡አለ።
ጅራፉም፡ዕድሜውም፡ሠላሣን፡ሳይሞላ።
ከተሰበሰቡት፡ከተመልካቾቹ፡
«የልብ፡ድካም፡ነው፡»አሉ፡አብዛኛዎቹ።
ፈላስሞቹም፡
«የሰው፡መጥፊያው፡ሴት፡ነች»አሉ።
አቤልን፡እነሡት፡ተዝካሩን፡ሲበሉ።

ኧረ፡ስንቱ፡ስንቱ፡ናቸው፡የሞቱቱ፡
ለንጉሣቸው፡ክብር፤ለባንዲራይቱ!



*እድሜ ለባለቅኔው አብዬ መንግስቱ ይሁንና እጅግ ከረቀቀ እና ከተዋበ ግጥማቸው*

*በቀዳማዊ ኃሥላሤ ዘመነ መንግስት ፣መንግስት የተባለው ተቋም ፣ተቀዳሚ ሥራው ግለሰባዊና ቡድናዊነትን በማንገስ ግለሰቦችን ከህግ በላይ ማደረግ ነበር፡፡ያም አካሄድ ሥሙን ቀየረ እንጂ መንፈሱ እየተንከባለለ ቀጥሎ ዛሬ ላይ ደርሰናል፡፡*

***በደምሳሳው፣ እኩል ፍትህ አልነበረም።የነበረው ገራፊነት፣ጨቋኝነት፣ፈላጭ ቆራጭነትና አምባገነንነት መሆኑንን ያለፈ ታሪካችን ጮሆ ይመሰክራል።***

*የዓለም ታሪክ እንደዘገበው ዓለማችን፣ የእኛን ዘራያቆብን ጨምሮ፣እስታሊን፣ሞሶሎኒ፣ሂትለር፣በአፍሪካ ደግሞ እነ ኢዲያሚን፣ጋዳፊና ቦካሳን አቅፎ ሌሎች እናንተ የምታወቋቸው በትረ መንግስትን የጨበጡ፣እጅግ አምባገነን፣ጨቋኝና ምህረት ቢስ ገራፊዎች ነበሯት፡፡...ከነሱ ሃሰብ በተቀራኒ ሆኖ ማሰብም ፈፅሞ የማይቻል እና ወደተለያየ የማሰቃያ ሥፍራ የሚስገባ ነበር፡፡*

*የራሰችንን የትላንት ታሪክ ይህንን እውነት የበለጠ ያስረዳናል፡፡፣ በራሰችን መንግስት እጅግ ወራዳና እና ዘግናኝ የግፍ ተግባር የሚፈፀምበት "ማእከላዊ የማሰቃያ እስርቤት"የሚባል ከደርግ ወደ ኢህአዴግ የተሸጋገረ ተቋም ነበረን፡፡ ወደ ሙዜምነት እነዲቀየር ከመወሰኑ በፊት አያሌ ንፁሃን ወድምና እህቶቻችን ተሰቃይተውበታል፡፡...*

*ያም ሆነ ይህ ትላንት መንግስት የተባለው ህዝብን እነዲያሥተዳድር በህዘብ ወይም በጉልበት ፈቃድ የአገዛዝ ሥልጣንን የያዘ ግለሰብና ቡድን ፣በወረቀት የተፃፈ ወይም ያልተፃፈ የመገረፍ፣የማሰቃየት፣በአደባባይም የመስቀልና የመረሸን መብት እነደነበረው አይካድም፡፡ ዛሬም በአንዳንድ ሀገሮች አለ፡፡*

*ከታሪክ የምንረደው አውነት፣መንግስት በአደባባይ ሰዎችን በሚዘገንን ሁኔታ በማሰቃይት ሲገድል ድርጊቱን በማወደስ በታላቅ ሆታና ፈንጠዝያ በጭካኔ የተሞላውን ድረጊት ያወደሱ ነበሩ፡፡...(መላውን የአንድ ሀገር ህዝብን ግን አየወክሉም)*

*ለምን እና እንዴት እንዳወደሱ፣ለአረመኔው አገዛዝ እንዳበዱለት እና እንዳረገዱለት፣በሥሜታዊነትም እንደሞቱለትም በዛሬ መነፅር ስናየው ግራ ይገባናል፡፡ ይሁን እነጂ በወቅቱ ቁጥሩ ትንሽ የማይባል ህዝብ በሶሻሊስትና በካፒታሊስት ጎራ ተከፍሎ እረስ በእርሱ ተጋድሏል፡፡*

*የእኛን የ1967 ዓ/ም ቱን ህዝባዊ አብዮትና የአብዮቱን አርጋዦችና አዋላጆች እንዲሁም፣በአጋጣሚው ድንገት ሥልጣን በእጃቸው የገባችላቸውን ደርጎች ፣የደርጎችንም ነፃ እርምጃና በኢሕአፓ ሥር ያሉት ወጣቶች የከተማ ትግል...ኢዲዩ፣ኢጫት፣መኢሶን፣አብዮታዊ ሰደድ፣ወዝሊግ የተባሉ ፓርቲዎች ሹኩቻ...ኢማሌዲህ፣እሰፓኮ፣ኢሠፓ... የአሥራ ሰባት አመት የህዝብ ድጋፍና፣ እነደተአምር የሚቆጠረውን የውርደት ስንብቱን ማስተዋል ብቻ የህዝብን ወቅታዊ ንቃትና በመሪዎች ሃሰብ የመጎዝን እውነት ይመሰክርልናል።*

*የግለሰቦች የሚያጓጓ ህይወትን ይቀይራል በእያንዳንዱ ዜጋ ላይ አወንታዊ ለውጥ ያስከትላል የተባለ ሃሰብ እንጂ፤ጠመንጃ ዋጋ እንደሌለው በተጨባጭ የሥገነዘበናል። ደርግ ብዙ ልማታዊ ሥራ ሳይሰራ ዕድሜ ልኩን ሀገርና ድንበር እያለ ባለው ተፈጥሯዊ ባህሪ ሙጭጭ ብሎ እነደበጋ ጉም ተኗል።*

*ደርግ በህዝብ አልገዛም ባይነትና በቀዝቃዛው ጦርነት ማከተም (እድሜ ለጎርቫቸው ይሁንና) ሰበብ የእብድ ገላጋይ በመጥፋቱ ምክንያትም ጭምር ነው እንደ በጋ ጉም የተነነው። ከዛስ...*

*ኢህአዴግ የሚባለው ገዢ በእርሱ እግር ተተካ።የኢህአዴግን ወደሥልጣን መምጣት የደገፈና የተቃወመ፣ ቢኖርም አብዛኛው ህዝብ ግን ደጋፊም ተቃዋሚም አልነበረም።ህዝቡ ፣ሁሉም ነገር በጥድፊያ እና በወከባ፣በላይ በላዩ ፣ድንገት እንደ ደራሽ ውሃ ሥለተከሰተበት ግራ ተጋብቶ ነበር።*

*ከዛስ? የብሔር ብሔረሰቦች የቋንቋ እኩልነት፣ ዴሞከራሲ ወዘተ። የሚለቱ ቋንቋ ገኖ ግን ደግሞ የቋንቋዎች እኩልነትን በማረጋገጥ በቋንቋ ሥም ክልሎች እነዲዋቀሩ በማደረግ፣ኢትዮጵያ የምትጋግረውን ኬክ ጥቂቶች ብቻቸውን እነዲያጋብሱ ማደረጊያ በር ከፈተ። "ከኢትዮጵያዊነትም በፊት ብሔር ይቅደም።"አለ።ሀገር ተከለለ።ክልል ሳይበግረው በሚኖረው ዜጋ ላይ ታላቅ ውዠንብርን በመፍጠር ጥላቻን በልቡ እነዲዘራ አደረገው። ይህ እና የተባለው የብሔር ብሔርብሔረሰቦች መብት በተነገረውና በተፃፈው ልክ ሊከበር ባለመቻሉና ገዢው ፓርቲ የወጣቱን የሥራ ጥያቄ በወጉ መመለስ ሥለአቃተው ለ23 ዓመት በእፎይታ የቆየው ኢህአዴግ በአራቱም ማዕዘን በተቃውሞ ተናጠ።*

***በመጨረሻም ሰው በዓለማዊ ሥርአት አስገዳጅነት ያለእውቀት፤ እነዲሁም***

***ዕወቀት በሚባለው መሳርያ፣በመሪነትና በተመሪነት ጎራ ቢመደብም፣የሰው ማህበራዊ፣፣ፖለቲካዊ፣ኢኮኖሚያዊ መብቱና ሰብአዊ ክብሩ በእኩልነት እስካልተከበረለት ጊዜ ድረስ በዚች ዓለም ላይ ዘላቂ ሰላም ከቶም እንደማይኖር በሚያስተምር መልኩ ኢህአዴግ በረሱ ውስጥ አብዮት ተፈጥሮ፣ የቸከለው የቋንቋ ግድብ ፈርሶ፣ ሰው ሰው ብቻ እና አንዳችም ልዩነት የሌለው መሆኑ ከራሱ ውሥጥ በተገኙት በለማ መገርሳና በዶ/ር አብይ አህመድ ተመሰከረ። በኢህአዴግ በራሱ ካንፕ ውስጥ "የሰውነት፣የእኩልነት፣የፍቅር፣የመተሳሰብና የመደመር አብዮት ፈነዳ።"ኢትዮጵያዊነት ሱስ መሆኑን አቶ ለማ መገርሳ አረጋገጡና የሁላችንንም አእምሮን አለሙት። በለውጡ መሪዎች ፈር ቀዳጅነትም፣የቋንቋ ፖለቲካ የአንድ ሀገር ዜጎችን ሰው መሆናቸውን አስረሥቶ እርስ በእረስ የሚያጋድላቸው መሆን እነደሌለበት በሰፊው ተሰበከ።***

*እያንዳንዱ የኢትዮጵያ ዜጋ እኩልና አንደኛው ከሌላው በፍፁም እነደማይበልጥና እነደማያንስም እነዲያምን እና ሲኖርም ኢትዮጵያዊ መሆኑን ሲሞትም ደግሞ ኢትዮጵያ ሆኖ ከአፈሯ ጋር እነደሚቀላቀል ተቀኘ።*

*የአብዮቱ መሪ ከኢህአዴግ ውስጥ ቢወጣም ፈጽሞ ከኢህአዴግ የተለየና በፈጣሪ እምነት ያለው በመሆኑ ይህንን ኃይማኖተኛ ህዝብ ፈፅሞ ቀየረው።*

*"እኔ ብቻ ልጠቀም ።እኔ ብቻ ልብላ።ሌላው ሰው ቢፈልግ አራት እገሩን ለምን አይበላም? የሚሉ አስተሳሰቦች በኣለም ላይ ከተንሰራፉ የዓለም ህመሞ ተባብሶ ሰው ሁሉ በፈጣን እና በሚዘገንን ሁኔታ ወደሞት መጎዙ አይቀሬ ይሆናል።"በማለት አብይ አህመድ በአብይነት ሰበከ።(ዛሬ በኢፊድሪ መንግስት በሱማሌ ብሔራዊ ክልል የሚንፀባረቀው ይኸው አውነት ነው።በቋንቋ የተመሰረተ ክልል የሚባል የልዩነት አውድ መሰረዝ አለበት።በምትኩም፣ በአፍመፍቻ ቋንቋ ሁሉም ዜጋ መጠቀሙ እነደተጠበቀ ሆኖ ሥያሜው እና የአስተዳደር ሥፈቱ ሊወሰን ይገባል።በሁሉም የሀገሪቱ ግዛቶች ሁሉም ዜጎች መኖርና ሰርተው መብላት እነዲችሉ ብቻ ሳይሆን ሀገሬ ነው ብለው ደፍረው እንዲናገሩ ልዩነትን የሚያጎላ ሥያሜ መቅረት ይኖርበታል። አዲሳባ፣ አዳማ ፣ድሬ፣አዋሳ፣በህር ዳር፣ጎንደር ወዘተ የጋራችን ነው። እያልንና ሀበት እያፈራንበት መቀሌ፣ጅጅጋ፤አሳይታ የኢትዮጵያዊያን ሁሉ ሀገር እንዳይሆኑ ለማድረግ በሰው ህሊና ውስጥ ጥላቻን መዝራት ተገቢ አይደለም፤ ብቻ ሳይሆን የሚያኑረንም አይደለም።*

)

ሰላማዊውንም አብዮት ለማና አብይ ከነደጉና ከነደመቀ ጋር "ሀ" ብለው ጀምረው ታሪክን ሙሉ ለሙሉ በመቀየር ኢትዮጵያ በአውነተኛ ፍትህ እንድትተዳደር በፍፁም ትህትና ህዝቡን ማገልገል እነደሚያስፈልግ ደጋግመው ተናገሩ።ከኢትየጵያ እስከ አሜሪካ።

የመሪዎች ሥግብግብነትና አልጠግብ ባይነት ሞት መኖርን ያለመገንዘብና ለትውልድ ደንታ ቢስነት ነው።በማለትም ከሶርያና ከጎረቤታችን ሱማልያና ደቡብ ሱዳን ልንማር ይገባናል በማለት፣ፍቅርና ይቅር ባይነት ብቻ ሳይሆን ሆደሰፊነትና አርቆ አሳቢነት በሁላችንም ልብ ውስጥ ይንገስ በማለትም ሰበኩ።

እርግጥ ነው፣ሥብከታቸው መሬት ጠብ የማይል ነው። "ጭካኔ የወለደው ስግብግብነት እና በዘረፋ የመበልፀግ ሩጫ ይቁም።አእምሮ ያላቸው እና ነገ አፈር መሆናቸውን በቅጡ የልተገነዘቡ ሰዎች ፤ በጉልበተኝነት በአስገዳጅ ዘዴ ተጠቅመው ዘርፈው እያበለፀጉ፣ ዜጎቻቸውን በችጋር እየገደሉ ነው።

በኢኮኖሚ ወደኋላ የቀረው ህዝብ ግን በእነሱ ሁሉን አቀፍ ስግብግብነት በችጋር እየተቆላና በተለያዩ መሰረተዊ ፈላጎት እጥረት ተሰንጎ የመከራን ንሮ እየገፋ ነው።ጥቂቶች ከሰው ይልቅ ገንዘብ እና ቅንጡ ኑሮ በልጦባቸው እንደእነሰሳ ለከርሳቸው በማድላት እነሱ በቁንጣን ተጨናንቀው ዜጋውን እያስረቡ ነው።"የሚል በእውነትና በመረጃ እና በማሥረጃ ላይ የተመሰረተ ነው።

ሰው በሰው በህሪ ውስጥ በማይገኝበት እና የሰውነት ፀጋውን በተገፈፈበት ሁኔታ ውስጥ ሚፈፅመው ድርጊት ከአራዊትነት ተርታ ያሰልፈዋል።የሰውነትን ባህሪ ከሚያሳጡ ነገሮች አነዱና ዋነኛው ሰው ሰው ሆኖ ሳለ ሰውነቱን ሲረሳና ራሱን ከሌላው ሰው እጅግ የበለጠ እና አምሳያው ከሱ አነፃር የሰውነት ሥያሜ ሊሰጠው አይገባም ብሎ ሲያምን ነው።ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ሂትለራዊ አስተሳሰብና አመለካከት ነው።ብእርግጥ እነ እስታሊንም ሆኑ ማኦ የረሳቸውን የመመለክያ ቲዎሪ በመፈጠርና በሚቃወማቸው ዜጋ ላይ ታርጋ በመለጠፍ አያሌ ንፁሃንን ረሽነዋል።መሰል ተግባረትም በየአህጉሩ በሚገኙ ሀገራት ሁሉ ተፈፅሟል።የአፍሪካ ግን የተለየና ዛሬም የቀድሞዎቹ ቅኝ ገዢዎች ቀብረው በወጡት የመከፋፈል ፈንጂ ደጋግማ የምትናጥ ከእወቀት፣ከእውነትና ከማስተዋል የራቀ ህዝብ የበዛባት አህጉር በመሆንዋ ተደጋጋሚ የእርስ

በእርስ መጠፋፋት ይከስትባታል።

በአፍሪካ በተለይም ዛሬ በሀገራችን በኢትየጵያ የአንድ በሃወርታዊ አገር ዜጋ ክልላዊ፣ብሔራዊና አለም አቀፋዊ ባህርያት እንዳለው እየታወቀ፣ይህንን እውነት ባለመገንዘብ ብቻ ሳይሆን በእያንዳንዱ ጎሳ ውስጥ ያሉ የበቁና የነቁ ገለሰቦች ፤ ለግል ጥቅማቸው ሲሉ ብቻ በህዝብ ውስጥ መረጋጋትና የሰከነ ሰላም እነዳይኖር ሁሌም፣በዘር፣በጎሳና በክልል ሰበብ በማድረግ ሲያሴሩ ይስተዋላሉ። ክልላዊ ባህሪንም የሙጥኝ በማለት ለብሔራዊና ለአለምአቀፋዊነት ባህሪ ጆሮ ዳባ ልበስ ብለዋል።

ለመሆኑ ክልላዊ፣ብሔራዊ እና ኣለምአቀፍ ባህሪ ምነድነው?

ክልላዊ ባህሪ የአንድ ቋንቋ ተናገሪነት፣በአንድ በተወሰነ ክልል ውሰጥ ጎልቶ በመገኘቱ በግል ሚታሰብ በህሪ ነው።‹‹ትግራዊነት ፣ኦሮሞነት፣አማራነት፤ሱማሌነት፣ጉራጌነት፣ከንባታነት፣ሲዳማነት፣ወዘተ። ቀጥታ ከቋንቋ ጋር የሚገናኙ የልዩነት ገጽታዎች ናቸው።(ግን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ሰውነትን የሚስክዱ አይደሉም። እኔ ሰው አይደለሁም። ትግሬ ነኝ።ኦሮሞነኝ።አማራነኝ።ሱማሌነኝ ።ወዘተ።ማለት ግን ያለመስተዋል ነው።ሰው ሰው እንጂ ቋንቋ ፈፅሞ ሊሆን አይችልም።ለንሮ ሲሉ በአንድ ሥፍራ በብዛት ሆነው አንድ ቋንቋ በመናገራቸው ሰው አይደሉም ቋንቋ ናቻው ለማለት ፈፅሞ አንችልም።) ይህን የክልላዊነት ባህሪ ብሔራዊ በህሪ ይገዛዋል።

ብሔራዊ ባህሪ በኢትዮጵያዊነት የሚገለፅ ባህሪ ነው።ኢትዮጵያዊነት፣አሜሪካዊነት፣ቻይናዊነት፣ራሻዊነት ወዘተ።ማለት ሲሆን ፣ገፅታው የወል ሃሰብን የያዘና የዜጎችን አበሮነት የሚሳይ ገፅታ በመሆኑ ግለሰቦችን ሁሉ በዜግነት አንድ ማዕድ እንዲቆርሱ ያደርጋቸዋል።

ዓላምአቀፋዊ ባህሪ ደግሞ ፣ሰው መሆን ነው።በቃ።እያንዳዳችን የዓለም አካል ነን።

ታዲያ ይህ አውነት ሆኖ ሳለ በእኛ ሀገር ሰዎች በቋንቋ ሰበብ ብቻ ለምን ይገዳደላሉ?እኛ ኢትየጵያዊያን እንዲህ የሚያናቁረን፣ሰውነታችንን እንድንዘነጋ ያደረገን በቋንቋ ላይ የተመሰረተ ግን በሁሉም በሔርና ብሔረሰቦች ውስጥ ሊተገበር የማይችል፣ ለጥቂት ገዢ መደቦች የቆመ የፖለቲካ ሥርአትና በደንብ ያለጠራው ህገመንግስታችን ሰበብ ሆኖን ነውን?

*እርግጥነው ይህ ቋንቋን ያነገሰ ፊደራሊዝም ፣ከሱማሊያ ፣ከኦሮሚያ ከትግራይና ከአማራ ክልል በሥተቀር ሌሎች አምስት ክልሎችን ብሔራዊ አደረጃጀት እነዲኖራቸው አድርጎ ሲያበቃ፣አማርኛ የሥራ ቋንቋቸው እንዲሆን አድርጓል።የሚገርመው ኢሕአዴግ(ገዢው ፓርቲ እንደ ኢሕአዴግ ሲሰበሰብ የሚወያየው እንደ ኢሕአዴግ ሆኖ ሳለ፣ከእረሱ በላይ ያለው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትም ስብሰባዎቹን በአማርኛ እያደረገ፣ለምንድነው የበዛው ኢትዮጵያዊ ለመግባባት የሚጠቀምበትን የጋራ ቋንቋውን ብሔራዊ ቋንቋ በማደረግ በሁሉም ክልሎች በኩል ደረጃ አማርኛ የሥራ ቋንቋ እነዲሆን ማደረግ ያዳገተው?*

*የእንጊሊዘኛ ቋንቋ ለእንጊሊዞች ብቻ እንደልተሰጠና የአለም ቋነቋ እነደሆነ ሁሉ አማርኛ የእኛ የኢትዮጵያዊያን ቋንቋ መሆን እነዴት ያደግተዋል?*

*በማስተዋል ከተመለከትን፣ ለቋንቋቸው ማደግ ከፍተኛ ተጋድሎ ያደረጉትን አንጊሊዝ፣ ፈረሣይን እና የአረብ ሀገራትን ትተን ቻይና እና ሩሲያ ቋንቋቸውን በአለም ላይ ለማሳወቅ የሚደርጉትን ጥረት በማደነቅ ብቻ አንቆምም ነበር።የእነሱና የእኛ ፣የሚለውን ኋላ አስቀሪ አመለካከትም ከህሊናችን በመፋቅ በኢትዮጵያ የሚነገሩ የ84 በሔረሰቦች ቋንቋዎች በሙሉ የዜጎች ሁሉ ነው።የእኛ ነው። ብለን እናምን ነበር።*

***አማርኛ የአማራ ነው።ትግሪኛ የትገሬ ነው።ኦሮምኛ የኦሮሞ ነው።ወዘተ።በማለት ሰውን በቋንቋ መጥራትና መከፋፈል ከቀጠልን የቋንቋን ምንነት ያልተረዳን ብቻ ሳንሆን ከቋንቋ ጋር አብረን እንደተወለድን የምናስብ ሆነናል።ይህ የተሳሳተ አስተሳሰብ ነው። ቋንቋ ስውና ሰውን ለማግባባት የተፈጠረ እነጂ ለመለያየት የተፈጠረ አይደለም።...***

*ለሀገራችን አስተማማኝ ደህንነት ሲባል የቋንቋ አምልኮ ከእኛ ከኢትዮጵያዊያን ፈፅሞ መወገድ ይኖርበታል።ቋንቋን ማምለክና በቋንቋ መታጠር ለዚህ እጅግ በቴክኖሎጂ ለተራቀቀ ክፍለ ዘመን የተገባ አይደለም።ጊዜ በማይበቃበትና ከባድ ሩጫና ተግባራዊ ክንውን በሚያስፈልገው ዘመነ ግሎባላይዜሽን እንደምንገኝም መርሳት የለብንም፡፤እንደሰማይ የራቁን ኃያላን ሀገሮች ወገብ ጋር እንኳ ለመደረስ ከእነሱ እጥፍ መሥራት እነደሚኖርብንም አንዘንጋ።የትላንትንም የውድቀት ታሪክ እናስታውስ።*

*ቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ "ቀኃሥ" የአገዛዝዎትን ፖሊሲ ቀይሩና እንደ እንጊሊዝ ዓይነት ፓርላማ እና የህዝብ አሥተዳደር በመፈጠር በሰላም ተከብረው ኑሩ። ቢባሉ "እንቢ! አሻፈረኝ "በማለትና*

*"በአጥንቴ ካልገዛው ሞቼ እገኛለሁ!" ብለው በመድረቃቸው፣መጨረሻቸው አላማረም።በእሳቸው ጦሥና ጥንቡሳስም የብዙ መልካም ሃሰቢዎች ህይወት ጠፋ።ንፁሓን ፀረ-ዓብዮት እየተባሉ ብቻ በግፍ ተገደሉ።(ደርጉ ለአብዮቱ ሲል ረሸናቸው ።በወቅቱ የነበረው ወጣትና ጎልማሳም እሰየው እያለ አጨበጨበ።)*

*ወያኒ ሥሙን ኢሕአዴግ አሰኝቶ በዘመቻ ዋለልኝ፤ቴዎድረስና ፒሊሱማ ውልቂጡማ ግንባር ቀደምትነት ሥልጣንን በኃይል ከደርግ ሲቀማ ፣የኢትዮጵያ ህዝብ የፍትህ፣የብለፅግናየዴሞክራሲ ጥማቴን ያረካልኛል ብሎ አጨበጨበ።(አጨበጨብን።አጨበጨብኩ። ) ለማለት ባንደፍርም፣ቢያነስ የብሔር ፖለቲካ ተጠቃሚ ያደርገኛል ብሎ ያሰበ እና ቋንቋ በደል አድርሶብኛል ብሎ የሚያምን ሁሉ በደንብ ማጭብጨቡን እኛ ብንክድ ኢቲቪ ይመሰክርብናል።...*

*ቀስ፣በቀስ ግን ኢሕአዴግ ፀረ ዴሞክራሲ እየሆነ በመምጣት "እኔ አውራ ነኝ !ሥራዬም ማስወለድ ነው።" በማለት እቅጩን በመናገሩ የነጻ ምርጫ ሃሳብ ገደል በመግባቱ የኢህአዴግ የመጀመርያው መጨረሻ ሆነ ።*

*ከጅምሩ ግን ኢሕአዴግ የሚጎዝበት መንገድ ትክክል እነዳልሆነ በወቅቱ እንደአሸን በፈሉ መፅሔቶች እና ጋዜጦች ላይ ይገለጽ ነበር። በነዚህ መጽሔቶች አማካኝነት ፓርቲው የሚጎዝበት መንገድ ሀገርና ህዝብን የማይጠቅም እነደሆነ፣በተባ እና በበሳል ብዕራቸው የተቹ፣እንደ የዓለም ሎሬት ፀጋዬ ገ/መድህን ቀዌሳ(ሀሁ ፐፑ የተሰኘውን ትያትር ያስተውሷል።)፣አሰፋ ጫቦ፣አበርሃም ያዬ፤ሐሰን ኡመር አብደላ፣ መራራ ጉዲና በሥማቸው።በብዕር ስም ደግሞ እነ ጎሞራው፣ፀጋዬ ገ/መድህን አርአያ፣ሥንሻው ተገኘ፣ ወዘተ።የኢሕአዴግን መንገድ በተደጋጋሚ በመተቸት፣ ለኢትዮጵያ የማየበጅና ተሪክና ባሃልን ብቻ ሳይሆን የአካባቢውንም ሆነ የዓለምን ሑኔታ ያላገነዘበ ነው።በማለት ተችተዋል። ወንዝ የማያሻገር አስተሳሰብንና አመለካከትን የሙጥኛ ማለቱን በተደጋጋሚ ገልፀው እነደነበር እናስታውሳለን።*

*የዓለምን የፖለቲካ ሁኔታ በተጨባጭ ያለመረዳትና በዓለም ላይ ከሚካሄደው ለውጥ ጋር አብሮ ያለመጎዝ የሚየስከትለው መዘዝ ብርቱ መሆኑን ዛሬ በኢህአዴግ ፓርቲ መሀፀን ውስጥ ተረግዞ የተወለደው የአብዮት መሪ፣በመገንዘብ ይቅርታና ፍቅር ሰውን ሁሉ ወደ አንድነትና*

*መተሳሰብ ያመጣል ብሎ በማመን የረሳነውን ፍቅርና ይቅር ባይነትን በልባችን እንዲሰርፅ በማድረጉ በሀገራችን በጎ ለውጥ እየታየ ነው፡፣*

*ግን ፣ግን በግለሰቦች ግትርነትና አርቆ ያለማሰብ የተነሳ ዛሬም በሀገራችን የበዙ ችግሮች ሊቀረፉ እንዳልቻሉና ይዘናቸው እየተጓዝን መሆኑን መዘንጋት የለብንም፡፡ከዚህ አንፃር ድግሞ ይህንን ሚያሳዝን እና እጅግ የሚያጓጓ የፍቅር የእኩልነት ፣የዴሞክራሲ፣የፈትህ፣የእውነት፣የበርሃን ፣የአንድነትና የመደመር ሃሰብን ይዞ ሚመራንን ሰው፣ጠ/ ሚ ዶ/ ር አብይ አህመድን በቅንነትና በታማኝነት ልንደግፈው ይገባናል፡፡*

*መሪነቱን አሜን ብሎ የተቀበለው እና ሙሉ ድጋፉን የሰጠው አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ልብ ውስጥ የተከለው የታላቅ ሀገር ህልም እውን እነዲሆንም ቅንና ቀና ነገር ሃሳቢ መሆን ይጠበቅብናል፡፡ በለውጥ አራማጁ ሀይል ፊት የተደቀነ ከባድ ችገር መኖሩንም መገንዘብና ማወቅ ጠንቆይ አያሰኝምና፣ችግሩን በማስተዋል ለመከላከልና ቀናው መንገድ አሸናፊ እነዲሆን፣ ከጠ/ ሚ ዶ/ ር/ አብይ አህመድ ጎን የኢትዮጵያ ህዝብ ሁሉ መቆም ይጠበቅበታል ብዬ አምናለሁ፡፡*

*የኢትዮጵያ ህዝብ እንደአንድ ሰው ሆኖ ፣ችግሩን ለማሶገድ መቆም ያለበት ፣ ችግሩ እጅግ ሥር የሰደደና ከ200 ዓመት በፊት የተፈፀሙትን ያካተተ በመሆኑ ነው፡፡ለመፍትሄው በጋራ መቆምና በአባት ሃጥያት ልጅ ሊቀጣ አይገባውም ማለት ያለበት፡፡በታሪክ የተፀፉ ብዙ አሉታዊ ሃሳቦች እና የጥላቻ መርዞች እስካሁንም ከህሊናችን አልጠፉምና እነሱን ከህሊናችን ማሶገድ ይገባናል፡፡*

*ይሁንና ዛሬ ይህንን ተውልድ የማይመለከቱ የዘር ማንዘር በደሎችን እያነሳን ባልሰራነው ወንጀል መወቃቀስ ከቀጠልን ከለውጡ ግንባር ቀደም አራማጆች በተፀራሪነት መሰለፋችንን መገንዘብ አለብን፡፡*

*ዛሬ ላይ የሥንቱ ዘር ከስንቱ ጋራ መደበላለቁን ስንቶቻችን ይሆን የምናውቀው? ይሁን እንጂ አብዛኛዎቹ የዘርና የቋንቋ ጉዳይ አቅንቃኞች ዛሬን በዛሬ መነፅር እንጂ ከመቶ አመት በፊት በተሰራ መነፅር አጥርቶ ማየት አልቻልንም፡፡ዛሬ ፣ዛሬን በዛሬ ዘመናዊ መነፅር ልናይ የሚገባን ወቅት ላይ ደርሰናል፡፡ ይህንን ለማደረግ ፍቃደኛ ባንሆን እንኳን የወቅቱ የሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ያስገድደናል፡፡እናም ያለፈ የሞተና የተቀበረ አሳፋሪ ድርጊት ከመቃብር እያወጣን*

*የንፁሃኑን ወጣት ህሊና በጥላቻ እነዲሞላ ላለማድረግ ለራሰችን ቃል እንግባ። ለሆዳችን በማድላትም ግትር አንሁን።*

*ሥንቶቻችን ነን ግትርነት የቀኃሥን(የቀዳማዊ ኃይለሥላሴን) ዓይነት ዋጋ እነደሚያስከፍል የምንገነዘበው? እድሜ ለለውጥ አራማጆቹ፣ለአቶ ለማ፣ ለዶ/ር አብይና ለጓደኞቻቸው እንበል እንጂ እጣ ፈንታችን ከቀኃሥም የከፋ ይሆን ነበር።ይህንን እውነት በመገንዘብ ዛሬም በማይረባ እና ለህዝብ በማይበጅና ፋይዳ ቢስ ሃሰብ ዙርዬ እየተነታረክን ጊዜያችንን ማጥፋት ብናቆም፣ለእኛም ለህዝብ እና ለሀገርም ይጠቅማል።*

*ሥለ ቋንቋም መግባቢያነት በቅጡ በመገንዘብና ቢያነስ ከአፍሪካዊያን ወንድሞቻችን በመማር የእኔ፣የእኔ ከማለት የኢትዮጵያዊያን ቋንቋ ሁሉ የእኛም ነው በማለት ሰማንያ አራቱንም ቋንቋዎች እንደራሳችን ቋንቋ በመቁጠር ለሁሉም ቋንቋ ክብር በመስጠት አሁን ሁላችንም የምንነጋገርበትን ወይም አብላጫው ህዝብ የሚግባበትን እንደራሳችን ቋንቋ በመቀበል ሀገራችንን በዓለም ፊት የራስዋ ፊደልና ቋንቋ ያላት ጥንታዊ ሀገር መሆንዋን እናስመስክር።ለሆድ ሞችነትና ተላላኪነት ይብቃን።*

*ለምንድነው አንዳአንድ አፍካዊያን ወድሞቻችን ኬንያን ጨምሮ፣ከራሰቸው ሀገር ህዝብ ቋንቋ ውጪ የባእዳንን ቋንቋ ፈረሳይኛና እንግሊዘኛን የሥራ ቋንቋ ያደረጉት?ለምንስ በዚህ ሰበብ የእርስ በእርስ ግጭት አለተፈጠረም?ለምንስ የእኛ ብሔረሰብ ቋንቋ ፣ለምን የስራ ቋንቋ አለሆንም? በማለት ሞተን እንገኛለን አላሉም? ይህንን ጥያቄ ከመለስን በእኛ ቋንቋ እጅግ ኩረት እንጂ ሀፍረት አይሰማንም።*

*በዚች ሀገር ከቶም የማይጠቅም ቋንቋ ተኮር ጉነጭ አልፋ ክርክር ማከተም ይኖርበታል።አንድ ብሔራዊ ቋንቋ እንደሚያስፈልገን ግን ኢትዮጵያዊያን ሁሉ የጋራ መግባባት ላይ መድረስ ይኖርብናል።ይህም ብሔራዊ ቋንቋ አማርኛ እነደሆነ በግሌ አምናለሁ።ምክንያቱም በሀገራችን ከጠረፍ እሰከ ጠረፍ የአማርኛ ቋንቋ ከመነገሩም በላይ የብዙዎቹ የክልል መንግስታት ቋንቋ አማርኛ በመሆኑ አማርኛን ብሔራዊ ቋንቋ ማደረግ እና የስራ ቋንቋዎቹን ግን በተጨማሪነት ተዳብለው እነዲሰሩ ማደረግ የወቅቱን የቋንቋ ውዥንብር በመፍታት ግጭቶችን ያስቀራል ብዬ ሥለማስብ ነው።*

*"በዘህ ወቀት፣ጊዜና ሰዓት፣አንድ ትልቅ የለውጥ ሃሳብ በሀገራችን ተወልዷል‹‹በዚህ የህዝብ ትልቅ ሃሳብ ልዕልና*

ሰንል አሮጌውንና የማያራምደንን ሃሰብ ከህሊናችን አውጥተን ልንቀብረው ይገባናል።ያ የምንቀብረውሃሳብ በዛ ዘመን ትልቅ እና ሁላችንንም የዘመርንልነት ቢሆን እንከዋ ለዛሬ የማይጠቅምና ዛሬችንን ብቻ ሳይሆን ነጋችንንም የሚያጨልምብን ከሆነ ለመቅበር ማወላወል የለብንም።የታላላቆቹን መንገስታት ታሪክ ተመልከቱ።ወደታሪክ አዙሪት ያልገቡትና ሁልጊዜም አዳዲስ እና የሚወደስ ታሪክን እየፃፉ የሄዱት ብዙሃኑ የሚጠቀምበትን ቋንቋም ሆነ መልካም ሃሳብ የራሰቸው በማደረግ ነው።

ቻይናን፣ሩሲያን፤ኩባን በአንድ ወገን፤ኢጣሊያንን፣እንጊሊዝን፣ፈረሳይን፣ጀርመንን በሌላ ወገን አደርጋችሁ ስታበቁ አሜሪካንና እስራኤልን ደግሞ በጋራ ተመልከቱ።ለትውልድ የሚተላለፍ ሥራ የሰሩት እጅግ በሚያስደንቅ የአንድነት እና የህበረት መነፈስ ነው።ለዛሬ ሥኬት የበቁት የታላቅ ሀገር ሥሜት እነዲኖራቸው ባደረጉ ታላላቅ መሪዎቻቸውም ጭምር ነው።በታላላቅ መሪዎቻቸው አርቆ አሳቢነትና የመሪነት ጥበብ መጥፎ ጅምራቸው በመጥፎነት አልቀጠለም።...

የአፍሪካ የታሪክ "ሰነድ ሲሰጣ" በውስጡ እጅግ "አሳዛኝ ጉዳጉድ" ይዞ እናገኘዋለን።አብዛኛው ግን የቅኝ ገዢዎች ታሪክ ነው። ያ ያለፈና በዚህ በ21ኛው መ/ክ/ዘ ተነስቶ የሚያወዛግበንም አይደለም።ታሪኩ ሲነበብም የራሱ ትልቅ የታሪክ ጉድፍ ያለውና በቅጡ ያልተጠና ቅኝ ገዢዎችም ለቀጣይ ሥራቸው ያመቻመቹትን እኩይ ሃሰብ በውስጡ ደብቆ የያዘ ነው። አውነትንም ያለነገሰ እና በቅኝ ገዢዎች እርሾ የተቦካ የዘረኝነት አስተሳሰብ፣ እነዲሁም በአድርባይ የታሪክ ፀሐፍያን ብዕር የሰከረ ህሊና የቀመረው አደገኛ መርዝ ነው። በአጭር አማርኛ።

እረግጥ ነው፤ ሁሉም ነገር ባለበት አይቆምም።ሰውም ሆነ ህይወት ያለው ነገር ሁሉ በለውጥ ሂደት ያልፋል።ሰው የፈጠረውም ቴክኖሎጂ በየጊዜው እየዘመነ ይሄዳል።ሁሉም የፖለቲካ ዓይነቶች በየጊዜው ይለዋወጣሉ።ምንም ነገር ባለበት አይቆምም። የዓለምን ፖለቲካ ዛሬ ላይ ሆነን፣በቅኝ ግዛትና በቀዝቃዘው ጦርነት ፖለቲካ አይን ለማየት መሞከር ፣በጭቃ በተለወሰ መስታወት የራስን ፊት እንደማየት ይቆጠርብናል።ግን፣ግን ሳይረፍድብን ወደቀልባችን በመመለስ ይህንን በጭቃ የተለወሰ የታሪክ መስታወት በማፅዳት መጪው ትውልድ (የልጅ ልጆቻችን) የሚኮሩበትና በፍቅር፣በመከባበር፣በአንድነት እጅ ለእጅ ተሳሰረው ወደብልፅግና የሚጎዙበትን መንገድ መጥረግ ለትውልዳችን የበጀል።

ትውልዳችን ያጎናፀፍነውን ብልጽግና በማድነቅ ለዘላለም እያወደሰ እሱም ከእኛ የተሸለች ሀገር ሀገሩ እንደትሆንለት እኛን በክብር እያታወሰ የሚጥርበትን የቅንነት ታላቅ የፍቅር ፣የቅንነት፣የመከባበር፣የትህትናና የአርቆ ሃሳቢነት ድልድይ እጅለእጅ ተያይዘን ለመገንባት ቃል እንግባ።

እንጂነር ሥመኝ በቀለ እንደሞተ ሁሉ እኛም ሞት አይቀርልንም።ሞት የሰው ሁሉ የማይቀር ፅዋ ነው።በፊታችን ሁሌም የተቀመጠ።አንድቀን ሳናስበው የምነጨልጠው ፅዋ ነው።ይህንን ፅዋ ቀናችን ደርሶም ሆኖ ሳይደርስ በድንገት ከመጨለጣችን በፊት ግን፣ዛሬ ቆም ብለን እነደናስብ የሚያደርግ አጋጣሚ ተፈጥሮልናል።በዚህ መልካም አጋጣሚ በመጠቀም ለተውልድ የሚተላለፍ መልካም ሥራ እንሥራ።እኛ ኢትዮጵያዊያን ጠንክረን በመስራት ወደጥንቱ መተባበራችን ካልተመለስን በአለም ፊት ሞገስ ያለን ህዝቦች መሆናችንን እንደገና ማስመስከር አንችልም።

የፈጣሪያችንን ዐይን በእንጨት እንዳንወጋው የሰጠንን መልካም አጋጣሚና ፍቃዱን እንጠቀም።በእውን ፈጣሪአችን ከዚህ በላይ ምን ያድርግልን?አሜሪካ ድረስ ሄዶ በጠላቶቻችን ፊት ራሳችንን በዘይቱ ቀባን፤እንባችንንም አበሰለን።ሰው መሆናችንንም አሳወቀን።ከእንግዲህ እኛ ኢትዮጵያዊያን ዘር፣ቀለም፣ጎሳና ኃይማኖት ሳንል ለፍቅር ተገዝተን ፣ፍትህ፣እኩልነት፣ዴሞክራሲ እና ብልፅግና ተሟልተው የሚገኙባትን ሀገር በጋራ እንገንባ።ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ህዝቧን

ይባርክ።

ሐምሌ 29/2010 ዓ/ም

አዳማ (ናዝሬት)

ተጻፈ